የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፵፭
አዲስ አበባ ግንቦት ፰ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝቦች ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17th Year No. 45
ADDIS ABABA 16th May 2011

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፳፩/፪ሺ፫
የወሎ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ..................... ገፅ ፭ሺ፰፻፴፪

## CONTENTS

Regulation No. 221/2011
Wello University Establishment Council of Ministers Regulation ....................... Page 5832

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፳፩/፪ሺ፫**

**የወሎ ዩኒቨርሲቲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፪ አንቀጽ ፭ እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ አንቀጽ ፭ (፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የወሎ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፳፩/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. መቋቋም**

፩/ ወሎ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል ።

፪/ የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል ።

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 221/2011**

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF WELLO UNIVERSITY**

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 5(1) of the Higher Education Proclamation No. 650/2009.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Wello University Establishment Council of Ministers Regulation No. 221/2011."

**2. Establishment**

1/ Wello University (hereinafter the "University") is hereby established as an autonomous higher education public institution having its own legal personality .

2/ The University shall be accountable to the Ministry of Education.

፫/ ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፲/፪ሺ፫ መሠረት ይተዳደራል ::

፫. ዋና ግቢ

የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በደሴ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል ::

፬. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ::

አዲስ አበባ ግንቦት ፰ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

3/ The University shall be governed by the Higher Education Proclamation No. 650/2009 and the Federal Universities Council of Ministers Regulation No. 210/2011.

3. **Main Campus**

The University shall have its main campus at Dessie and may establish elsewhere other academic units and centers of research and community services.

4. **Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 16th day of May 2011.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA